## ትምህርት 14

### የእግዚአብሔር ቃል (መጽሐፍ ቅዱስ) ክፍል 1

መጽሐፍ ቅዱስ ከ40 በላይ በሆኑ ጸሐፊዎች 2000 ዓመታት በላይ በሚሆን ጊዜ ውስጥ በ3 በዕብራዊያን፣ በአራማይክና በግሪክ ቋንቋዎች የተጻፈ ነው።

በአሁኑ ጊዜ እንደ ሚታየው መፅሐፍ ቅዱስ በአንድነት የተጠረዘ መጽሐፍ ብቻ አልነበረም። የብሉይም ሆነ የአዲስ ኪዳን 66ቱ መጻሕፍት ሁሉ ለየብቻ ትናንሽ መጽሐፍት ነበሩ። ከዚህም ሌላ የእግዚአብሔርን ሃሳብ የሚገልጡ ተቀባይነት ያላቸው የብሉይና የአዲስ ኪዳን መፃሕፍት በእግዚአብሔር ዕርዳታ ለመለየት በተለያዩ ጊዜያት የዓለም የክርስትና እምነት መሪዎች ጉባኤዎች አካሂደዋል። የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን በተመለከተ፣ አይሁዳዊያን የእግዚአብሔር ተከታዮች ከእግዚአብሔር የሆኑት መልዕክተኞች/ነቢያት ለይተው ያውቋቸው ስለ ነበር የጻፏቸውንም መጻሕፍት የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው አድርገው ተቀብለዋቸዋል። የብሉይ ኪዳን የቀኖና መጻሕፍት ብዙት በጌታ ኢየሱስና በሐዋሪያቱ አገልግሎት ጊዜም ተለይተው ይታወቁ ነበር። በ250 ዓ.ም. በተደረገው የክርስትና እምነት መሪዎች ጉባኤ እነዚሁ 39 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የእግዚአብሔር መንፈስ እንዳለባቸው ሙሉ በሙሉ ዕውቅና አግኝተው ተቀብለዋቸዋል። ነገር ግን በዚህ ጊዜ ተጨማሪ የቀኖና መጻሕፍት በሚባሉት ዙሪያ በአንድ ሃሳብ መስማማት ያልተቻለ ሲሆን እስካሁንም ድረስ ተቀባይነታቸው ላይ ወደ አንድ ስምምነት አልተደረሰም። እንዲያውም ወንጌላዊያን ቤተ-እምነቶች ማናቸውም አፖክሪፋ (ተጨማሪ የተቀኖና መጻሕፍት) የእግዚአብሔር መንፈስ የሌለባው ናቸው ብለው ስለሚያምኑ አይቀበሉዋቸውም።

በ393 ዓ.ም. በሂፖ ሪገስ (የአሁኑ አናባ - አልጄሪያ) እና በ397 ዓ.ም. ካርቴጅ (ቱኒሲያ) ላይ በተካሄዱት የክርስትና መሪዎች ጉባኤዎች 27ቱ የአዲስ ኪዳን ቀኖና መጻሕፍት ሁሉ በእግዚአብሔር ዕርዳታ አማካይነት ዕቅውና (ተቀባይነት) አግኝተው ስምምነት ላይ ተደርሷል።

እነዚህ መጻሕፍት የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው መሆኑን ለመለየት እንደ መስፈርት የተወሰዱት፡ -

1. ደራሲው ነብይ ወይም ሐዋሪያ እንዲሁም ከሐዋሪያ ጋር የቅርብ ግንኙነት በነበረው የእግዚአብሔር አገልጋይ በተለይም አዲስ ኪዳን ከሆነ፣ በመጀመሪው ክፍለ ዘመን ጌታ ኢየሱስ በምድር ያገለግል ከነበረበት ወቅት ብዙ ባልራቀ ጊዜ የተጻፈ መሆኑን፤ (ማርቆስ ከጴጥሮስ ጋር፤ ሉቃስ ከጳውሎስ ጋር እንደ ነበራቸው ግንኙነት ካለው ሰው ለማለት ነው)
2. በመጽሐፉ ይዘት በአብያተ ክትስቲያናት በስፋት ተቀባይነት አግኝቶ ጥቅም ላይ እየዋለ ያለ መሆኑን፤
3. መጽሐፉ ከሌሎች ተቀባይነት ካገኙ ቅዱሳት መጻሕፍት ጋር የማይጻረር/የሚጣጣምና ጤናማ አስተምህሮ የያዘ መሆኑ፡
4. መጽሐፉ የእግዚአብሔርን መንፈስ አሰራር የሚያሳይ ስነ-ምግባራዊና መንፈሳዊ ኃይል የሚንጸባርቅ መሆኑ ናቸው።

ቅዱስ ጀሮም ለመጀመሪያ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን ከግሪክ ወደ ላቲን ቋንቋ የተረጎመና 39 የብሉይ ኪዳን 27 የአዲስ ኪዳን በጠቅላላው 66ቱን መጻሕፍት በአንድነት አጠቃልሎ የያዘ ቩልጌት የተባለ አንድ ጥራዝ መጽሐፍ ቅዱስ በ405 ዓ.ም. ላይ አዘጋጅቶ የጨረሰ የስነ-መለኮት አጥኚ ሰው ነው።

ተጨማሪ የቀኖና መጻሕፍት (Apocrypha) የሚባሉት በወንጌላዊያን ቤተ እምነቶች ተቀባይነት ያላገኙበት ምክንያት ዝርዝር ከ27 በላይ ሲሆን ከእነዚህ መካከል ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል፡-

1. ከ66ቱ የቀኖና መጻህፍት አስተምህሮና ልምምዶች ጋር የሚቃረን ትምህርት ያለባቸው መሆኑ። ለምሳሌ ብንወስድ የቀኖና መጻህፍት መዳን የሚገኘው በእግዚአብሔር ጸጋ በእምነት አማካይነት መሆኑን ሲያረጋግጡ ተጨማሪ የቀኖና መጻሕፍት ግን መዳን በሥራ የሚገኝ ነው የሚል መሆኑ።
የግሪኩ ቃል Kanon- measurement (መለኪያ/መመዘኛ) የሚል ትርጉም አለው።
2. በአይሁድ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ ያልተካተቱ (የሌሉ) መሆኑ። የአይሁድ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ብዛት 39 ሲሆኑ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ግነ በጠቅላለው አይቀበሉዋቸውም።

3. በ400 ዓመታት የጸጥታው ዘመን (በትንቢተ ሚልኪያስ መጽሐፍና በመጥምቁ ዮሐንስ መካከል በነበረው ዘመን) ውስጥ የተጻፉ መሆናቸው። በእነዚህ የጸጥታው ዓመታት ምንም ዓይነት ከእግዚአብሔር የሆነ መልዕክት በነቢያት አማካይነት ያልመጣበት (አግዚአብሔር አንድም ነብይ ያላስነሳበት) ጊዜ በመሆኑ ነው።
4. ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም ሆነ ሐዋሪያቱ ከእነዚህ መጻሕፍት በመጥቀስ ያላስተማሩ መሆኑን።
5. ትክክለኛ የአግዚአብሔር ሃሳብ ያለበት ቃል ከተገኘባቸው ያው በቀኖና መጻሕፍት የሰፈረን ዕውነት መደጋገም ነው እንጂ የተለየ ጠቃሚ መልዕክት ያለው ክፍል በውስጣቸው አለመኖሩ ነው።
6. አብዛኞቹ የአፖክሪፋ መጻሕፍት የተጻፉት በግሪክ ቋንቋ ሲሆን የብሉይ ኪዳን የቀኖና መጻሕፍት ግን የተጻፉት በእብራይስጥና በአራማይክ ቋንቋዎች መሆኑ ናቸው።

እውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል የሆኑት የብሉይና የአዲስ ኪዳን 66ቱ መጻሕፍት በሰው ሰራሽና የሐሰት ትምህርት ሳይበረዙ እንዲቆዩ በእውነተኛ የአግዚአብሔር ቃል አገልጋዮች ብዙ ስራ ሲሰራ የቆየ ሲሆን በተለይም የፕሮቴስታንት ቤተ-እምነት መሪዎች በእግዚአብሔር ቃል በመመስረት ያዘጋጁት "THE 5 SOLAs" በመባል የሚታወቀው መሰረታዊ የእምነት መግለጫ ታላቅ ጠቀሜታ ያለው ነው።

ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስና ከሐዋሪያቱ የክርስትና አስተምህሮ በኂላ እያደር ከአዲስ ኪዳን አስተምህሮ ፈቀቅ ያሉ ሰው ሰራሽ ትምርቶች ከየአካባቢው ብቅ ብቅ በማለት ታይተዋል። በ16ኛው ክፍለ ዘመን በአውሮፓ ውስጥ በሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት፣ መሰል ከአዲስ ኪዳን የሚጻረር ትምህርትና ድርጊት ተስፋፍቶ ነበር። በዚህ ጊዜ ወደ መጀመሪያውና ትክክለኛው የጌታ ኢየሱስና ሐዋሪያቱ አስተምህሮ እንመለስ የሚል በማርቲን ሉተር የተጀመረው የፕሮቴስታንት የተሃድሶ በኂላም በሌሎች እንደ ኡልሪክ ዙዊንግሊ (ስዊትዘርላንድ)፣ ጆን ካልቪን (ፍራንስ)፣ ጆን ኖክስ (ስኮትላንድ) ያሉ የወንጌላዊያን ተሀድሶ መሪዎች አማካኝነት እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ቀጥሎ ድነትን በሚመለከት 5 ወሳኝ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆዎች/ነጥቦች የሚያካትት በላቲንኛ Five Solas በመባል የሚታወቅ መሰረታዊ የአምነት አቋም መግለጫ ወጣ። ይህ የሆነው የወቅቱ የሮም ካቶሊካዊት ቤተ-ክርስቲያን አነርሱ ያዘጋጁት መታወቂያ ካርድ ያልገዛ፣ በስራው ቅዱስ ያልሆነ ... ወዘተ ከእግዚአብሔር የዘለዓለም ሞት ፍርድ አይድንም በማለትና ሌሎችም በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተመሰረቱ በርካታ ትምህርቶች ያስተምሩ ስለነበር ነው።

የ Five Solas ድነትን በሚመለከት በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት አስተምህሮ ላይ የተመረኮዙ መሰረታዊ የእምነት አቋም መግለጫዎች የሚከተሉት ናቸው።

By Grace alone (Sola Gratia) በጸጋ ብቻ
Through Faith alone (Sola Fide) በእምነት ብቻ
In Christ alone (Solus Christus) በክርስቶስ ብቻ
According to Scripture alone (Sola Scriptura) እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ
For God's Glory alone (Soli Deo Gloria) ለእግዚአብሔር ክብር ብቻ

መዳን የሚገኘው፡ -

1. **በጸጋ ብቻ**፡ - ድነት በእግዚአብሔር ለሰው የተሰጠ ነጻ ስጦታ ነው። ለሰው የተሰጠውም በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ነው እንጂ ኃጢአተኛው ድነት ማግኘት የተገባው ወይም የሚያስችለው ፍጹም የሆነ የራሱ የጽድቅ ስራ ስለ ነበረው አይደለም የሚል ነው። ማስረጃ ጥቅሶች እነሆ፡ -

    ሮሜ 3፡10-12፣ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፤ “ጻድቅ ማንም የለም፤ አንድም እንኳ፤ 11 አስተዋይ የለም፤ እግዚአብሔርንም የሚሻ አንድም የለም። 12 ሁሉም ተሳስተዋል፤ በአንድነት የማይጠቅሙ ሆነዋል፤ በጎ የሚያደርግ ማንም የለም፤ አንድም እንኳ።”
    ኤፌ 2፥5፣ “በበደላችን ሙታን ሆነን ሳለ፣ በክርስቶስ ሕያዋን አደረገን፤ የዳናችሁት በጸጋ ነው።”
    ኤፌ 2፡8-9፣ በእምነት፣ በጸጋ ድናችኂልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ 9 ማንም እንዳይመካ በሥራ አይደለም፤
2. **በእምነት ብቻ**፡ - ክርስቶስ ኢየሱስ እስከ መስቀል ሞት ድረስ መስዋዕት በመሆን የሰራው የጽድቅ ስራ የእኛ ጽድቅ ተደርጎ እንዲቆጠር ያከናወነው መሆኑን በማመናችን ብቻ ነው ጻድቅ ተደርገን የተቆጠርነው የሚለው።

ሮሜ 4፡4-5፣ አንድ ሰው ሥራ ከሰራ ደመወዙ እንደ ስጦታ ሳይሆን እንደ ተገቢ ዋጋው ይቈጠርለታል። [5] ነገር ግን ለማይሠራው፣ ኃጥኡን ሰው ጻድቅ በሚያደርግ በእግዚአብሔር ለሚያምን ሰው፣ እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቈጠርለታል። (ሮሜ 3፡28)
ገላ 3፥8 "መጽሐፍ፣ እግዚአብሔር አሕዛብን በእምነት እንደሚያጸድቅ አስቀድሞ በማየት፣ "አሕዛብ ሁሉ በአንተ ይባረካሉ" በማለት ወንጌልን ለአብርሃም አስቀድሞ አስታወቀው።"
ሉቃ 23፡39-43 ይህ ወንጀለኛ መጽደቅ የቻለው በእውነተኛ ንስሃና እመነቱ ባይሆን ኖሮ በወንጀሉ ሞት ተፈርዶበት የነበረ አይደለምን በማለት ቄስሌይ ተናግሯል።

3. **በክርስቶስ ብቻ፡-** በክርስቶስ ኢየሱስ አማካይነት ካልሆነ በስተቀር ሰው ከዘለዓለም ሞት ፍርድ በምንም ዓይነት መዳን የማይችል መሆኑን የሚያመለክት ነው። ከኃጢአታችን የተነሳ ይጠብቀን የነበረው የዘላለም ሞት ፍርድና ስቃይ ክርስቶስ ኢየሱስ በእኛ ምትክ ሆኖ እንደ ኃጢአተኛ ፍርዳቸንና ስቃያችን በቀራንዮ መስቀል ላይ እርሱ ባይቀበል ኖሮ ሌላ ማምለጫ ፈጽሞ እንደ ሌለ የሚያስረዳ ነው።

   ዮሐ 14፥6፣ "ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ "መንገዱ እኔ ነኝ፤ እውነትና ሕይወትም እኔው ነኝ፤ በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።"
   ሮሜ 10፥9፣ "ኢየሱስ ጌታ ነው" ብለህ በአፍህ ብትመሰክር፣ እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን፣ ትድናለህ።"
   ሐሥ 4፥12፣ "ድነት በሌላ በማንም አይገኝም፤ እንድንበት ዘንድ ለሰዎች የተሰጠ ከዚህ ስም በስተቀር ሌላ ስም ከሰማይ በታች የለምና።"
4. **እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ፡ -** ለክርስትና እምነት፣ ሁሉም የቤተ-ክርስቲያን ልማዶች (ተራዲሽንስ)፣ የሃይማኖት መግለጫዎችና (ክሪድስ) አስተምህሮዎች (ቲቺንግስ) የ66ቱ መጻሕፍት ስብስብ የሆነው ሙሉ ስልጣን ያለው መጽሐፍ ቅዱስ ቃል ጋር የሚስማሙ/የማይቃረኑ መሆን አለባቸው የሚል ነው። (ከዚህ መጽሐፍ የሚቃረን አሳብ ያለው አሰተምህሮም ሆነ አመራርና አሰራር ጳጳሳት ወይም የቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ ጉባኤ ሊያዘጋጁ/ሊያካሄዱ አይችሉም። ደግሞም ፕሮቴስታንቶች መሰረታዊ የድነት ትምህርትን በሚመለከት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሰፈረው ትምህርት ግልጽ ስለሆነ ጳጳሱና ለዚህ ተመርጠው የተመደቡ አስተማሪዎች ባይሆኑም ምዕመናን በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ መረዳትና መተርጎም ይችላሉ የሚል ከካቶሊኮች የተለየ አቋም አላቸው ።)
   ይሄ ለቤተ-ክርስቲያን ሕይወት ታላቅ ጠቀሜታ ያለው የማዕዘን ድንጋይ ነው። እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚመራው/የሚያስተዳድረው በቃሉ ነው። የጳጳሳት ሃሳብና የቤተ-ክርስቲያን ልማዶች (ትራዲሽንስ) ቤተ-ክርስቲያንን ሊመሩ አይገባም። ቤተ-ክርስቲያን በእግዚአብሔር ቃል ስትመራ በእግዚአብሔር በራሱ እየተመራች ነው ማለት ነው። በቤተ-ክርስቲያን ላይ ሙሉ ስልጣን ያለው የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው።

   2 ጢሞ 3፡16-17፣ ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው፤ ለማስተማር፣ ለመገሠጽ፣ ለማቅናት በጽድቅም መንገድ ለመምከር ይጠቅማሉ፤ [17] ይኸውም የእግዚአብሔር ሰው ለመልካም ሥራ ሁሉ ብቁ ሆኖ እንዲገኝ ነው።
   2 ጴጥ 1፥21፣ "ምክንያቱም ትንቢት ከእግዚአብሔር የተላኩ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ተናገሩት እንጂ ከቶ በሰው ፈቃድ የመጣ አይደለም።"
5. **ክብሩ ለእግዚአብሔር ብቻ፡ -** የእግዚአብሔር አገልጋዮች ለሰው የተገባውን አክብሮት ቢቸራቸውም፣ የተጋነነና ከመጠን ያለፈ ክብር ለፍጥረታት (ለማርያም፣ለመላዕክት፣ ለቅዱሳን …ወዘተ) ሊሰጥ የማይገባ ሰለሆነ ክብሩ ለእግዚአብሔር ብቻ መሆን አለበት የሚል ነው። ስለዚህ ፍጥረት እንደ ፍጥረትነቱ ይከበራል፣ ለእግዚብሄር የተገባው ክብር ግን ለእግዚአብሔር ብቻ ሊሰጥ ይገባል። እግዚአብሔር ለአንድ አገልጋይ ትልቅ የጸጋ ስጦታ ቢሰጠው አገልጋዩን እንደ እግዚአብሔር ማየት አይገባምና። ድነት በፈቃዱ ያመጣውና ለድነትም የሚያበቃ ስራ ያከነው ራሱ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

   ሮሜ 11፥36፣ "ሁሉም ከእርሱ፣ በእርሱ፣ ለእርሱ ነውና፤ ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።"

1 ቆሮ 10፥31 “እንግዲህ ስትበሉም ሆነ ስትጠጡ፣ ወይም ማንኛውንም ነገር ስታደርጉ፣ ሁሉንም ነገር ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት”

1 ጴጥ 4፥11፣ “ከእናንተ ማንም የሚናገር ቢኖር እንደ እግዚአብሔር ቃል ይናገር፤ የሚያገለግልም ቢኖር እግዚአብሔር በሚሰጠው ብርታት ያገልግል፤ ይኸውም እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት እንዲከብር ነው፤ ክብርና ኀይል ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ይሁን፤ አሜን።”
ቲቶ 3:4-5, ነገር ግን የአዳኛችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ፍቅር በተገለጠ ጊዜ፣ [5] ስላደረግነው የጽድቅ ሥራ ሳይሆን፣ ከምሕረቱ የተነሣ አዳነን። ያዳነንም ዳግም ልደት በሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ መታደስ ነው፤

**የእግዚአብሔር ቃል**

**የእግዚአብሔር ቃል በግሪክኛ ሁለት ዓይነት መጠሪያዎች አሉት፡-**

**ሎጎስ**፡- በመጻሕፍት የሰፈረው ቃል ሲሆን የዘላለም የማይቀያየር የእግዚአብሔር የልብ ሀሳብ ነው፡፡ እግዚአብሔር ተጽፎ እንዲቀመጥልን ያደረገው እኛ አውቀነው አምነን እንድንድንበትና ተግባር ላይ አውለነው በእግዚአብሔር የተዘጋጀልን በረከት ሁሉ መውረስ እንዲያስችለን ለኛ ጥቅም ሲል ነው፡፡ ሎጎስ የሚለው ቃል የሚገኙባቸው ሉቃ 8፡11፣ ፊሊጵ 2፡16፣ ዕብ 4፡12
ጌታ ኢየሱስም በዮሐ 1፡1 ሎጎስ ተብሏል፡፡
**ሬማ**፡- ደግሞ እግዚአብሔር ድምጽ በማሰማት የተናገረው/የሚናገረው ቃል ነው፡፡ እግዚአብሔር በተለያዩ ዘመናት በድምጽ ተናግሯል፡፡ ነገር ግን የተናገረው ቃሉ ሁሉ አልተጻፈም፡፡ እግዚአብሔር ራሱ (አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ) ወይም በነቢያት፣ በቃል አገልግሎት አቅራቢዎች፣ በምክር ሰጪዎች አማካይነት ለግለሰብ ወይም ለብዙ ሰዎች ስለ አንድ የተለየ ጉዳይ ምሪት ለመስጠት የሚመጣ ነው፡፡
**የእምነት ቃል** (ወርድ ኦፍ ፌይዝ)፡- ይሄ ግን አንድ የእግዚአብሔር አገልጋይ ወይም ማንኛውም አማኝ፣ በጽሁፍ ከሰፈረው ወይም በድምጽ ከተነገረው የእግዚአብሔር ቃል ወስዶ በእምነት/አምኖ ለራሱም ሆነ ለሌሎች በድምጽ ሲናገር የእምነት ቃል ይባላል፡፡ ሮሜ 10፡8-10፣ 2ቆሮ 4፡13፡፡

በመጻሕፍት የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ስልጣን ያለው ቃል ነው፡፡ ስልጣን/ኦቶሪቲ/ የሚለው ቃል የመጣው "auther" ከሚለው ቃል ነው፡፡ የአንድ የጽሁፍ ስራ ስልጣን የሚወሰነው በደራሲው ስልጣን ልክ ነው፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ደራሲ አምላክ የሆነው መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ያስረዳል፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ስልጣን ደግሞ ሙሉ መለኮታዊ ስልጣን ነው፡፡ ስለዚህ የመጽሀፍ ቅዱስ ስልጣን የመንፈስ ቅዱስ ስልጣን ያህል ነው፡፡ መጽሀፍ ቅዱስን መጋፋት መንፈስ ቅዱስን ስልጣን መጋፋት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በህይወታችን ዘርፍ ሁሉ ሙሉ ስልጣን አለው፡፡ በቤተ-ክርስቲያን አመራር አካላትና ምእመናን ሁሉ ላይ ሙሉ ስልጣን አለው፡፡ የአመራር አካላቱና አገልጋዮች ሁሉ የቃሉ አገልጋዮች ናቸው እንጂ ቃሉን የመለወጥ ስልጣን የላቸውም፡፡

የእግዚአብሔር ቃል ስልጣን ያለው መሆኑን አመልካች ጥቅሶች፤ 2ጴጥ 1፡20-21፤ 2ጢሞ 3፡16-17

የእግዚአብሔር ቃል ትክክለኛ ፍቺ መስጠት የሚችለው ራሱ መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ አንድ ሰው ስለሰራው የጽሁፍ ስራ (መጽሐፍ) በ.. ገጽ ላይ እንዲህ ብሎ ያሰፈረው አረፍተ ነገር ምን ለማለት ፈልጎ ነው ተብሎ ቢጠየቅ ከማንም በላይ ትክክለኛ መልስ መስጠት የሚችለው ራሱ ደራሲው ብቻ ነው፡፡ ምክንያቱም ምን ለማለት ፈልጎ እንደጻፈው ያውቃልና፡፡

ማቴ 5፡17-18 ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን መጻህፍት አንዲት ትንሽዋ ፊደል ሳይቀር የማይሻር ስልጣን ያለው መሆኑን ተናግሯል/አጽድቋል፡፡

ዮሐ 14፡25-26፣ 16፡12-14 እነዚህ ጥቅሶች አዲስ ኪዳንም ልክ እንደ ብሉይ ኪዳን በመንፈስ ቅዱስ ደራሲነት መጻፋቸውን ያስረዳል፡፡

**የእግዚአብሔር ቃል ኃይል**

- ኃይል የእግዚአብሔር ነው፣ 1ዜና 29፡11፣ መዝ 62፡11፣ ራእ 19፡1 ፡፡ እግዚአብሔር ኃይሉን በተለያዩ ነገሮች ውስጥ ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ የፍጥረታት ኀይል ሁሉ (የእርሱ ኃይል ማከማቻዎች ናቸው) የተገኘው ከእግዚአብሔር ነው፡፡ ኃይል ከእርሱ ይመነጫል፡፡ በፈለገው ጊዜ ለወደደው ነገር ይጠቀምበታል፡፡ የእግዚአብሔር ኃይል ማከማቻዎች ከሆኑት ነገሮች አንዱ የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡
- ኤር 23፡29 ቃሌ እንደ እሳት አለቱንም እንደሚያደቅ መዶሻ አይደለምን?
- ዘፍ 1፡1-31፣ መዝ 33፡6-8 ሰማይና ምድርን በውሳጣቸው ያለውን ፍጥረት ሁሉ ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣ/የመፍጠር፤ ሪከሪኤት የማድረግ፣ ኃይል አለው፡፡
- ዕብ 12፡26-27 ሰማይና ምድርን የማናወጥ የፈጠረውንም መልሶ የማፍረስ/የማደስ ኃይል አለው፡፡
- ኢሳ 55፡11 እግዚአብሔር ማድረግ የፈለገውን ሁሉ በቃሉ መስራት/ማድረግ ይችላል፡፡
- ሮሜ 1፡16 በወንጌል (በወንጌሉ ቃል) አላፍርም፡፡ ምክንያቱም ለሚያምን ሁሉ ለድነት የሚሆን የእግዚአብሔር ኃይል ነው፡፡

**የእግዚአብሔር ቃል ባህርይ**

- ማቴ 24፡35፣ ኢሳ 40፡8፤ የማይለዋወጥና የማያልፍ ለዘላለም ጸንቶ የሚኖር ነው፡፡ ዮሐ 10፡35 የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸውን አማልክት ካላቸውና መጽሐፍም ሊሻር የማይቻል ከሆነ…
- ቃሉ ባዶውን/ብቻውን ሳይሆን ከመንፈሱ ጋር ነው፡፡ 1ተሰ 1፡5 ወንጌላችን ወደ እናንተ የመጣው በኃይልና በመንፈስ ቅዱስ በብዙም መረዳት እንጂ በቃል ብቻ አይደለም፡፡ መዝ 33፡6
- ዕብ 4፡12 የእግዚአብሔር ቃል፡
  ህያው የሆነ የሚሰራና ኃይል ያለው ነፍስንና መንፈስን መለያየት የሚችል በሁለት አፍ እንደተሳለ ሠይፍ የልብን አሳብና እቅድን/ምኞትን የሚመረምር…. ስንማረው የራሳችን ሕይወት ምን እንደሚመስልና ምን መምሰል እንደሚገባው የሚያሳየን፡፡ መስታወት የውጭው ሰውነታችንን የእግዚአብሔር ቃል ግን ውስጣዊ ሰውነታችን (ልባችንና አእምሯችን ውስጥ) ያለውን ምንም ሳይቀር ያሳየናል፡፡
- ምሳ 30፡5 የእግዚአብሔር ቃል ሁሉ እንከን የለበትም (ፒዩር)፤ እርሱ ለሚታመኑበት ሁሉ ጋሻቸው ነው፤ መዝ 12፡6 የእግዚአብሔር ቃል የጠራ ቃል ነው፡፡ ሰባት ጊዜ እንደተጣራ በምድር ላይ በከውር እንደተፈተነ ብር ነው፡፡ ተፈትኖ የጠራ/እንከን የሌለበት እውነት ነው፡፡
- ዮሐ 17፡17 ቃልህ እውነት ነው፡፡ በእውነትህ ቀድሳቸው; የዕውነት ቃል ኤፌ 1፡13፣ ቆላ 1፡5
- መዝ 18፡30 የአምላክ መንገድ ፍጹም ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል የነጠረ ነው፡፡ መጠጊያ ለሚያደርጉት ጋሻ ነው፡፡

**ወንጌል የሚጠራባቸው የተለያዩ ስሞች፡ -**

ሀ. የሕይወት ቃል፣ ዮሐ 6፡68፣ ሐሥ 7፡8፣ ፊሊጵ 2፡16
ለ. የሚያድን ቃል፣ ሐሥ 11፡14
ሐ. የምስራች ዜና፣ ሉቃ 2፡8-11
መ. የዕውነት ቃል፣ ኤፌ 1፡13
ሠ. አዲስ ኪዳን፣
ረ. የክርስቶስ/የሐዋሪያት አስተምህሮ፣
ሰ. የእግዚአብሔር ቃል፣ ተብሏል

**የእግዚአብሔር ቃል እንከን (ስህተት) የለበትም ሲባል ምን ለማለት ነው፡፡**

- ባህርይንና አስተሳሰብን ከመግራቱ/ከማስተካከያነቱ አንጻር ቅዱስ/ምቹ ነው፡፡ ሁሉም ቢቀበለውና ቢኖርበት ዓለምን ሁሉ በሰላም በፍቅር በመተሳሰብ የሚሞላ በአንድ ቤተሰብ አባልነት የሚያኖር ነው፡፡
- በህግነቱ ፍጹም ትክክለኛና በፍርዱም ፍጹም ፍትሀዊ ነው፡፡
- በተስፋነቱ ቸርነት የተሞላ ነው፤
- ስለ ወደፊት በሚተነብየው ነገር መፈጸም ፍንክች የማይል/የማይታጠፍ መፈጸሙ የማይቀር ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ በምድራዊ ሕይወቱ ያደረገው ሁሉ ያደረገው አስቀድሞ የተነገረ የእግዚአብሔር ቃል እንዲፈጸም ነው፡፡ (18 ያህል ናቸው)

- በእውነትነቱ ፍጹም የጠራ/የነጠረ/የተረጋገጠ/100 በመቶ እውነተኛ ነው፡፡ ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ በሁሉም ረገድ ሙሉ እምነት የሚጣልበት ነው፡፡ በሙሉ እምነት ልንቀበለው ስራ ላይ ልናውለው ጠላት ሲፈትነን መልስ ልንሰጥበት የተገባ ነው፡፡ ጠላት ግን እንድንጠራጠረውና ቀስ በቀስ ችላ እንድንለው እንድንተወው ይፈልጋል፡፡ቃሉ ፍጹም እውነት ቢሆንም ካላመኑት ለሰው ህይወት በረከት አያስገኝም፡፡
  መጽሐፍ ቅዱስ ለማጥፋት በተለያየ ጊዜ በተለያዩ ተዋጊዎችና የውጊያ መሳሪያዎች በስነ ጽሁፎች፣ በፈላስፎች ፍልስፍና፣ በተቃራኒ እምነቶችና በሳይንስ ግኝቶች የተከፈተበት ዘመቻ ሁሉ ሳይበገር ጥሶ እያለፈ እየሰራ ያለ ነው፡፡

**የእግዚአብሔር ቃል ዋጋ (ቫልዩ) ምን ያህል ነው**

መዝ 19፡7-11 እጅግ ውድ ነው፣ ታላቅ ወሮታም ያስገኛል፡፡ የእግዚአብሔር ቃል የእግዚአብሔር ጥበብና ማስተዋል ነው ምሳ 3፡13-18፣ 8፡7-10-11፣ 16፡16፣ ኢዮ 28፡12-19

መዝ 138፥2, “ወደ ቅዱስ መቅደስህ እሰግዳለሁ፤ ስለ ምሕረትህና ስለ ታማኝነትህ፣ ለስምህ ምስጋና አቀርባለሁ፤ ስምህንና ቃልህን፣ ከሁሉ በላይ ከፍ ከፍ አድርገሃልና።”

መዝ 119፥72, “ከአእላፋት ብርና ወርቅ ይልቅ፣ ከአፍህ የሚወጣው ሕግ ይሻለኛል።”

የእግዚአብሔር ቃል (የአግዚአብሔር ጥበብና ማስተዋል ነው- ምሳ 2፡1-2) ከምንፈልጋቸው ነገሮች ሁሉ እጅግ የላቀ ተፈላጊና ውድ ነው፡፡ ዋጋው በምድራዊ ሀብት ሁሉ ሊመዘን የማይችል ወሰን የሌለው ታላቅ ነው፡፡

እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ከሰጣቸው እጅግ ውድ ስጦታዎች አንዱ ቃሉ ነው፡፡ በወረቀት የተጻፈው መጽሀፍ ቅዱስ በትንሽ ገንዘብ ስለምንገዛ (የመጽሐፍ ቅዱስ አፕ በነጻ ስለምናገኝ) የቃሉ ዋጋ ቀላል አድርገን እንዳናየው ያሻል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ስንገዛ የምንከፍለው ገንዘብ ለሕትመት የወጣለትን ዋጋ ነው እንጂ ቃሉ እግዚአብሔር ራሱ በነጻ ባይሰጠን ኖሮ በብዙ ዋጋም አናገኘውም ነበር፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ የጠቅላላው የሰው ዘር ሁሉ የተናጠልና የወል ችግር ትክክለኛ መንስኤና መፍትሔ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ብቸኛ መጽሐፍ ነው፡፡

የእግዚአብሔር ቃል በእምነትና ስራ ላይ በማዋል ወደ ሚያስፈልገን ነገር ሁሉ የምንመነዝረው የበረከታችን ሁሉ ማከማቻ ነው (በረከታችን ሁሉ አጣምሮ የያዘ/የተሞላ) ነው፡፡

©ኤልያስ ታሪኩ (ዶ/ር)                    2018 ዓ. ም.